# መመሪያ ቁጥር 1094/2017

# የነዳጅ አቅርቦት፣ ሥርጭት፣ ግብይት እና አጠቃቀምን ለመቆጣጠር የወጣ መመሪያ ቁትር 1094/2017

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር በነዳጅ ውጤቶች ግብይት አዋጅ ቁጥር 1363/2017 አንቀጽ 28(2) በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ **"የነዳጅ አቅርቦት፣ ሥርጭት፣ ግብይት እና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 1094/2017"** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1/ "አጓጓዥ" ማለት የተለያዩ የማጓጓዣ ዘዴዎችን በመጠቀም የነዳጅ ውጤቶችን ከኢትዮጵያ ውጭ ከሚገኙ ማከማቻዎች ሀገር ውስጥ ወደሚገኙ ዴፖዎች፣ ማደያዎች ወይም ለቀጥታ ተጠቃሚዎች የሚያጓጉዝ ድርጅት ነው፤

2/ "የነዳጅ ማጓጓዣ" ማለት የነዳጅ ውጤቶችን ከኢትዮጵያ ውጭ ከሚገኙ ማከማቻዎች ሀገር ውስጥ ወደሚገኙ ዴፖዎች፣ ማደያዎች ወይም ለቀጥታ ተጠቃሚዎች የሚያጓጉዝ ካልብሬት የተደረገ የነዳጅ ቦቴ ተሽከርካሪ ሲሆን ለነዳጅ መያዣነት ተብሎ የተሠራ በጎማ የሚሽከረከር መጎተቻ ብረት ያለው አነስተኛ ታንከርን ይጨምራል፤

3/ "ካሊብሬት" ማለት የነዳጅ መለኪያ መሳሪያዎችን የልኬት መጠን በተወሰነው የደረጃ መስፈርት መሰረት ዝግጁ ማድረግ ነዉ፤

4/ “ዲስፔንሰር” ማለት የነዳጅ ውጤቶችን ከነዳጅ ማከማቻ ታንከር ወደ ተሽከርካሪ የሚያስተላልፍ ማሽን ነዉ፤

5/ “ፍሎ ሜትር ” ማለት በዲስፔንሰር ላይ የሚገኝ ዲጂታል የነዳጅ መጠን መለኪያ መሳሪያ ነዉ፤

6/ “አዋጅ” ማለት የነዳጅ ውጤቶች ግብይት አዋጅ ቁጥር 1363/2017 ነው፤

7/ በአዋጁ አንቀጽ 2 ትርጉም የተሰጣቸው ቃላት ለዚህ መመሪያም ተፈጻሚ ይሆናሉ፤

8/ በዚህ መመሪያ በወንድ ጾታ የተገለጸው ሴትንም ይጨምራል፡፡

### 3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ ከወደብ እስከ ነዳጅ ችርቻሮ ድረስ ባለው የነዳጅ ውጤቶች አቅርቦት፣ ሥርጭት፣ ግብይትና አጠቃቀም የግብይት ሰንሰለት በተሰማሩ የግብይት ተዋናዮች እና ተቆጣጣሪ አካላት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የግብይት ተዋንያን ግዴታ</u>

### 4. <u>የአስመጪ ግዴታ</u>

ማንኛዉም አስመጪ አግባብነት ባለዉ ሌላ ህግ የተጣለበት ግዴታ እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

1/ ከባለሥልጣኑ በሚላክለት የአጓጓዦች፣ የነዳጅ ማጓጓዣዎች እና የነዳጅ ማደያዎች ዝርዝር እና ሌሎች መረጃዎች መሠረት ብቻ የነዳጅ ጭነት ፈቃድ የመስጠት፤

2/ እያንዳንዱ የነዳጅ ማጓጓዣ ጂፒኤስ የተገጠመለት መሆኑን አረጋግጦ አገልግሎት የመስጠት፤

3/ ቀጣይ ጭነት ከመፍቀዱ በፊት የነዳጅ ማጓጓዣው አሽከርካሪ ከወደብ ወይም ከማሰራጫ ዴፖ የጫነውን የነዳጅ ውጤት ለታለመለት መዳረሻ አድርሶ ስለማስረከቡ በመረካከቢያ ሰነድ የማረጋገጥ፤

4/ የነዳጅ ማጓጓዣው ጉዞ ከመጀመሩ በፊት የአከፋፋዩን ዓርማ እና የጭነት መዳረሻ የሚያመላክት ጽሑፍ መለጠፉን የማረጋገጥ፤

5/ የነዳጅ ውጤቶች የጭነት ሰነዶችን አሟልቶ የመስጠት፤

6/ የየዕለቱን የነዳጅ ውጤቶች ጭነት የሚመለከት ሪፖርት በደብዳቤ ወይም ለዚሁ ዓላማ በተዘረጋው የኤሌክትሮኒክ መገናኛ ሥርዓት ለባለሥልጣኑ እና ለሚኒስቴሩ በ24 ሠዓት ውስጥ የማስተላለፍ፤

7/ ከባለሥልጣኑ በሚደርሰዉ የጽሁፍ መረጃ መሰረት የታገደ አከፋፋይ፣ የነዳጅ ማደያ፣ አጓጓዥ ወይም ማጓጓዣ አገልግሎት እንዳያገኝ የማድረግ፡፡

5. <u>የአከፋፋይ ግዴታ</u>

ማንኛውም አከፋፋይ አግባብነት ባለዉ ሌላ ህግ የተጣለበት ግዴታ እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

1/ ማንኛውም የነዳጅ ማደያ የሀገሪቱን እና የአከፋፋዩን የጥራት ደረጃ እንዲሁም የደህንነት መስፈርቶች አሟልቶ የተገነባ መሆኑን አረጋግጦ ዉል የመግባት፤

2/ በስሩ የሚገኝ የነዳጅ ማደያ የሚጠቀምባቸው ዲስፔንሰሮች እና ሌሎች የመለኪያ መሳሪያዎች በየዓመቱ ካሊብሬት መደረጋቸውን የማረጋገጥ እና ሲበላሹም የመጠገን፤

3/ ሥራ ባቆመና በጥገና ላይ ባለ የነዳጅ ማደያ ስም የነዳጅ ውጤቶች ጭነት እና ሽያጭ ያለማካሄድ፤

4/ በአንድ የነዳጅ ማደያ ስም የተጫነን ነዳጅ ለሁለት የነዳጅ ማደያዎች ማካፈል ካስፈለገ በሁለቱም ስም የጉዞ ሰነድ /FDC/ ላይ ተመዝግቦ እንዲጫን የማድረግ፤

5/ በስሩ በሚገኝ የነዳጅ ማደያ የሚከናወነው የነዳጅ ግብይት ክፍያ በባለስልጣኑ እዉቅና በተሠጠዉ ብሄራዊ የነዳጅ መገበያያ ሥርዓት ብቻ መፈፀሙን የመከታተልና ጉድለት ያለበትን ለይቶ ለባለስልጣኑ የማሳወቅ፤

6/ በስሩ የሚገኝ የነዳጅ ማጓጓዣ ጭኖ ከመውጣቱ በፊት የአከፋፋዩን ዓርማ እና የጭነት መዳረሻ የሚያመላክት ጽሑፍ መለጠፉን እና የተሟላ የጭነት ሰነድ መያዙን የማረጋገጥ፤

7/ የጭነት ስምሪት ትዕዛዝ ሲሰጥ የእያንዳንዱን የነዳጅ ማጓጓዣ ብቃት፣ የመንገዱን ርቀት እና ሁኔታ በማገናዘብ የመድረሻ ጊዜውን ወስኖ አሽከርካሪው ጉዞ ከመጀመሩ በፊት ለዚሁ ዓላማ በተዘረጋው የኤሌክትሮኒክ የመገናኛ ሥርዓት ለባለሥልጣኑ የማሳወቅ እና ባስቀመጠው መድረሻ ጊዜ ስለመድረሱ ክትትል የማድረግ፤ ከተቀመጠው የጊዜ ገደብ በላይ ዘግይቶ በሚደርስ አሽከርካሪ ላይ አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ለባለሥልጣኑ እና ለአጓጓዡ የማሳወቅ፤

8/ ከወደብና ከማሰራጫ ዴፖ የተጫነው ነዳጅ በታለመለት የመዳረሻ ቦታ መራገፉን የማረጋገጥ እና ይህንኑ እያንዳንዱ ወር በተጠናቀቀ በ5 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ የማሳወቅ፤

9/ የነዳጅ ማጓጓዣው አሽከርካሪ የጫነውን የነዳጅ ውጤት ለታለመለት መዳረሻ ቦታ በትክክል ማድረሱንና ማራገፉን ሳያረጋግጥ ቀጣይ ስምሪት ያለመስጠት፤

10/ የነዳጅ ማጓጓዣ አሽከርካሪ በተፈቀደለት የጉዞ መስመር እና ከሌሊቱ 10 ሰዓት እስከ ምሽቱ 1 ሰዓት ብቻ መጓዝ እንዳለበት ትእዛዝ የመስጠትና ክትትል የማድረግ፤

11/ የነዳጅ ማጓጓዣው አሽከርካሪ ከተፈቀደለት የጉዞ መስመር ወይም ሠዓት ውጭ ሲጓዝ ወይም ከታለመለት መዳረሻ ቦታ ውጪ ሲያራግፍ የተገኘ እንደሆነ በአጓጓዡ ላይ በውሉ መሠረት እርምጃ በመውሰድ ይህንኑ ለባለሥልጣኑ የማሳወቅ፤

12/ የመዳረሻ ስምሪት ለውጥ ሲያስፈልገው በቂ ምክንያት መኖሩን በማረጋገጥና ማስረጃ በማያያዝ በደብዳቤ ወይም ለዚሁ ዓላማ በተዘረጋው የኤሌክትሮኒክ መገናኛ ሥርዓት ባለሥልጣኑን ጠይቆ የማስፈቀድ፤

13/ በወደብ፣ በመንገድ እና በመዳረሻ ቦታዎች በነዳጅ ማጓጓዣ ላይ አደጋ ሲከሰት መንስኤዉን በመለየት በ24 ሠዓት ውስጥ በደብዳቤ ወይም ለዚሁ ዓላማ በተዘረጋው የኤሌክትሮኒክ መገናኛ ሥርዓት ለባለሥልጣኑ የማሳወቅ፤

14/ ከወደብ የተጫነውን እና በታለመለት መዳረሻ የተራገፈውን የነዳጅ ዓይነትና መጠን በተመለከተ እያንዳንዱ ወር በተጠናቀቀ በ5 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ለባለስልጣኑ በጽሁፍ ሪፖርት የማቅረብ፤

15/ በስሩ ለሚገኙ የነዳጅ አንጓዦች እና የነዳጅ ማደያዎች ስለነዳጅ ውጤቶች አያያዝ፣ ደህንነት፣ የፍሳሽ አወጋገድ እና ሌሎች ተዛማጅ ሙያ ነክ ጉዳዮች የስልጠና ድጋፍ የመስጠት፤

16/ በስሩ አዲስ የተቀላቀለ የነዳጅ አንጓዥ፣ ማጓጓዣ ወይም የነዳጅ ማደያ ሲኖር ሥራ ከመጀመሩ በፊት ለባለሥልጣኑ በጽሁፍ የማሳወቅ፤

17/ በስሩ የሚገኝ የነዳጅ አንጓዥ፣ ማጓጓዣ ወይም የነዳጅ ማደያ በተለያየ ምክንያት ሥራ ሲያቆም እንዲሁም ወደ ሥራ ሲመለስ ይህንኑ ለባለስልጣኑ የማሳወቅ፤

18/ የእያንዳንዱን የነዳጅ ማደያ እና የነዳጅ ማጓጓዣ አሽከርካሪ ሙሉ መረጃ አደራጅቶ የመያዝ እና የሥራ አፈጻጸሙን የመከታተል፣ የማብቃትና የአሠራር ጉድለት ያለበትን ለአንጓዡ እና ለባለሥልጣኑ በጽሁፍ የማሳወቅ፤

19/ በስሩ ያለ የነዳጅ አንጓዥ ወይም የነዳጅ ማደያ ውሉን ለማቋረጥ ሲጠይቅ ከዕዳ ነጻ ስለመሆኑ ክሊራንስ ሲያቀርብ በውላቸው መሠረት መልቀቂያ የመስጠት፡፡

6. <u>የነዳጅ ማደያ ግዴታ</u>

ማንኛውም የነዳጅ ማደያ አግባብነት ባለዉ ሌላ ህግ የተጣለበት ግዴታ እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

1/ ባለሥልጣኑ በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ የነዳጅ መጠን መለኪያ ፍሎ ሜትር በማደያው የማስገጠም፤

2/ የሚጠቀምባቸውን ዲስፔንሰሮች እና ሌሎች የነዳጅ መለኪያ መሳሪያዎች በየዓመቱ ካሊብሬት የማስደረግ እና አግባብነት ባለው ተቆጣጣሪ አካል የሚሰጠውን የማረጋገጫ ምልክት በመሳሪያዎቹ ላይ የመለጠፍ፤

3/ የነዳጅ ማጓጓዣው እሽጉ ያልተላጠና ትክክል መሆኑን አረጋግጦና በፍሎ ሜትር አስለክቶ የነዳጅ ውጤቶችን ከአሽከርካሪው በመረካከቢያ ሰነድ የመረከብ፤ ስለመረከቡ ማስረጃ የመስጠት፤

4/ በተጫነለት እና በተረከበዉ የነዳጅ ውጤት መካከል የመጠን ልዩነት ካጋጠመ ተረክቦ ልዩነቱን በ12 ሠዓታት ውስጥ በደብዳቤ ወይም ለዚሁ ዓላማ በተዘረጋው የኤሌክትሮኒክ የመገናኛ ሥርዓት ለአከፋፋዩ የማሳወቅ፤

5/ በባለሥልጣኑ ዕውቅና በተሰጠው የዲጅታል መገበያያ ሥርዓት ብቻ በመጠቀም የነዳጅ ውጤቶች ሽያጭ የመፈፀም፤

6/ ዋጋ የተተመነላቸውን የነዳጅ ውጤቶች መንግሥት በሚያወጣው የመሸጫ ዋጋ የመሸጥ፤

7/ በማደያው የነዳጅ ውጤት ካለው ለተጠቃሚዎች ያልተቋረጠ የሀያ አራት ሰዓት አገልግሎት የመስጠት፤

8/ በኤሌክትሪክ መቋረጥ ምክንያት አገልግሎቱ እንዳይቋረጥ ጀነሬተር የመትከል፤

9/ የነዳጅ ጭነትና ርክክብ ሰነዶችን አሟልቶና አደራጅቶ የመያዝ እና በተቆጣጣሪ አካላት ሲጠየቅም የማቅረብ፤

10/ የነዳጅ መቅጃ መሳሪያዎች በሙሉ ለአገልግሎት ዝግጁ እንዲሆኑ የማድረግ፡፡

## 7. <u>የአጓጓዥ እና የባለንብረቶች ማህበር ግዴታ</u>

ማንኛውም አጓጓዥ ወይም የባለንብረቶች ማህበር አግባብነት ባለዉ ሌላ ህግ የተጣለበት ግዴታ እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

1/ የነዳጅ ማጓጓዣው በየዓመቱ ካልብሬት ተደርጎ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው መሆኑን የማረጋገጥ፤

2/ ዕያንዳንዱ የነዳጅ ማጓጓዣ ወደ ስምሪት ከመግባቱ በፊት ጂ.ፒ.ኤስ የተገጠመለት መሆኑን የማረጋገጥ፤

3/ በስምሪት ላይ ባሉ የነዳጅ ማጓጓዣዎች ላይ አከፋፋዮች አርማቸውን እና የጭነት መዳረሻዎችን የሚያመላክት ጽሑፍ እንዲለጥፉ ትብብር የማድረግ፤

4/ የነዳጅ ማጓጓዣውን ስምሪት የመከታተልና ችግሮች ሲያጋጥሙ በፍጥነት የማስተካከያ እርምት የመውሰድ፤

5/ የነዳጅ ውጤቶች የማጓጓዝ ሂደት አሳማኝ ባልሆነ ምክንያት እንዳይስተጓጎል ተገቢውን ክትትል እና ድጋፍ የማድረግ፤

6/ አሽከርካሪው የነዳጅ ማጓጓዣውን በተፈቀደለት የጉዞ መሥመር ብቻ ማንቀሳቀሱን እና በታለመለት መዳረሻ ማራገፉን የማረጋገጥ፤

7/ አሽከርካሪው የነዳጅ ማጓጓዣውን ከሌሊቱ አስር ሠዓት እስከ ምሽቱ አንድ ሠዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ብቻ ማንቀሳቀሱን የማረጋገጥ፤

8/ በነዳጅ ማጓጓዣ ላይ ከአሽከርካሪው፣ ከረዳቱ እና ከነዳጅ ውጤቶች በስተቀር ሌላ ሰው እና ዕቃ እንዳይጫን ክትትል የማድረግ፤

9/ እያንዳንዱ የነዳጅ ማጓጓዣ አሽከርካሪ የሥራ ብቃት እና ዲሲፒሊን ያሟላ መሆኑን አረጋግጦ ቅጥር የመፈጸም፤

10/ የነዳጅ ማጓጓዣዎችን እና አሽከርካሪዎችን መረጃ አሟልቶና አደራጅቶ የመያዝ እና በተቆጣጣሪ አካላት ሲጠየቅም የማቅረብ፡፡

## 8. <u>የነዳጅ ማጓጓዣ አሽከርካሪ ግዴታ</u>

ማንኛውም የነዳጅ ማጓጓዣ አሽከርካሪ አግባብነት ባለዉ ሌላ ህግ የተጣለበት ግዴታ እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

1/ በባለሥልጣኑ በተለየ ሁኔታ ካልተፈቀደለት በስተቀር የነዳጅ ማጓጓዣውን በተፈቀደለት የጉዞ መስመር እና ከሌሊቱ አስር ሠዓት እስከ ምሽቱ አንድ ሠዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ብቻ የማንቀሳቀስ እና የነዳጅ ውጤቶችን በተፈቀደለት የመዳረሻ ቦታ ብቻ የማራገፍ፤

2/ የጫነውን የነዳጅ ውጤት እሽጉ ሳይላጥ በጥንቃቄ በመያዝ ለታለመለት የመዳረሻ ቦታ የማድረስ እና በፍሎ ሜትር አስለክቶ የማስረከብ፤

3/ ከቀጣዩ ስምሪት በፊት የጫነውን የነዳጅ ውጤት ለታለመለት መዳረሻ ስለማስረከቡ የርክክብ ሰነድ ለአከፋፋዩ የማቅረብ፤

4/ የነዳጅ ማጓጓዣውን ስምሪት ለመቆጣጠር የሚገጠሙትን ጂፒኤስ እና ሌሎች መሣሪያዎች በጥንቃቄ የመያዝ እና ሲበላሹም ወድያውኑ የማስጠገን፤

5/ በነዳጅ ማጓጓዣው ላይ ከአሽከርካሪው፣ ከረዳቱ እና ከነዳጅ ውጤቶች በስተቀር ሌላ ሰው እና ዕቃ ያለመጫን፤

6/ የነዳጅ ውጤት ጭኖ በሚንቀሳቀስበት ጊዜ ሁሉ የተሟላ የጉዞ ሰነድ ይዞ የመንቀሳቀስ እና በተቆጣጣሪ አካላት ሲጠየቅም የማሳየት፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>ስለቁጥጥር</u>

9. <u>በሚኒስቴሩ ስለሚደረግ ቁጥጥር</u>

በሌሎች ሕጎች የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው ሚኒስቴሩ የሚከተሉትን የቁጥጥር ተግባራት ያከናውናል፡-

1/ባለሥልጣኑ ያዘጋጀዉን የነዳጅ ዋጋ ቀመር መርምሮ ከውሳኔ ሀሳብ ጋር ለመንግስት ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

2/ ባለስልጣኑን እና አግባብነት ያላቸውን አካላት በማስተባበር አዲስ የሚገነቡ የነዳጅ ማደያዎች በመላ ሀገሪቱ ፍትሐዊ ስርጭትንና ተደራሽነትን ያማከሉ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

3/ በመላ ሀገሪቱ የነዳጅ አቅርቦት፣ ሥርጭት፣ ግብይት እና አጠቃቀም የተሳለጠ እንዲሆን ባለስልጣኑን እና የሚመለከታቸውን አካላት ያስተባብራል፡፡

10. <u>በባለሥልጣኑ ስለሚደረግ ቁጥጥር</u>

በሌሎች ሕጎች የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው ባለሥልጣኑ የሚከተሉትን የቁጥጥር ተግባራት ያከናውናል፡-

1/ አስመጪው በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች መሠረት የነዳጅ ጭነት አገልግሎት የሚሰጥ መሆኑን ይቆጣጠራል፤

2/ ወደ ሥምሪት የገቡና ስምሪት ያቋረጡ አንጓዦችን፣ የነዳጅ ማጓጓዣዎችን እና ማደያዎችን ዝርዝር መረጃ ከአከፋፋዮች በመቀበል አፈጻጸሙን ይቆጣጠራል፤

3/ ወደ ስምሪት የሚገባ እያንዳንዱ የነዳጅ ማጓጓዣ በየዓመቱ ካልብሬት ተደርጎ የምስክር ወረቀት የተሰጠው እና ጂ.ፒ.ኤስ የተገጠመለት መሆኑን ያረጋግጣል፤

4/ የነዳጅ ውጤቶችን ከወደብ ወይም ከማሰራጫ ዴፖዎች ጭነው የወጡ የነዳጅ ማጓጓዣ አሽከርካሪዎች በተሰጣቸው የሥምሪት መስመር እና የጊዜ ገደብ መጓዛቸውን እንዲሁም በታለመላቸው መዳረሻ ቦታ ደርሰው ማራገፋቸውንና ህጋዊ ርክክብ መፈጸማቸውን ይከታተላል፤

5/ ማንኛውም ማደያ የሚጠቀምባቸው ዲስፔንሰሮች እና ሌሎች የመለኪያ መሳሪያዎች በህግ ሥልጣን በተሰጠው ተቆጣጣሪ አካል በየዓመቱ ካሊብሬት መደረጋቸውን ይቆጣጠራል፤

6/ የነዳጅ ውጤቶች ግብይት ክፍያዎች በኤሌክትሮኒክ የመገበያያ ስርዓት ብቻ እንዲፈጸሙ ያደርጋል፣ አፈፃፀሙን ይቆጣጠራል፤

7/ ከማደያ ውጭ ነዳጅ ለመቸርቸር የሚያስችል ህጋዊ ፈቃድ ከተሰጠው ሰው እና የመሸጫ ቦታ ውጭ የነዳጅ ውጤቶችን ሲሸጥ በተገኘ ሰው ላይ ነዳጁን በመውረስ ለመንግስት ገቢ የማድረግና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን አስተዳደራዊ እርምጃዎች ይወስዳል፤

8/ የግብይት ተዋናዮች በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ የተደነገጉትን ግዴታዎች በአግባቡ መፈፀማቸውን ይከታተላል፣ ግዴታቸውን ባልተወጡ ላይ ተገቢውን አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፡፡

## 11. <u>አግባብነት ባለው አካል ስለሚደረግ ቁጥጥር</u>

በሌሎች ሕጎች የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው አግባብነት ያለው አካል የሚከተሉትን የቁጥጥር ተግባራት ያከናውናል፡-

1/ ወደ ክልሉ በየቀኑ የሚላኩትን የነዳጅ ውጤቶች የስርጭት መረጃ ከአስመጪው በማሰባሰብ ለተላከላቸው የነዳጅ ማደያዎች ደርሰው በአግባቡ መራገፋቸውን እና ርክክብ መፈጸሙን ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፤

2/ የዞን፣ የወረዳ እና የክፍለ-ከተማ ንግድ ጽህፈት ቤቶች የነዳጅ ውጤቶች አቅርቦትና ስርጭት በተቀመጠው አሰራር መሰረት ተግባራዊ ስለመሆኑ ክትትልና ቁጥጥር እንዲያደርጉ ያስተባብራል፣ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

3/ ከነዳጅ ማደያ ውጭ ነዳጅ ለመቸርቸር የሚያስችል ህጋዊ ፈቃድ ከተሰጠው ሰው እና የመሸጫ ቦታ ውጭ ማንኛውም ሰው ነዳጅ እንዳይሸጥ ይከታተላል፣ ይህን ድንጋጌ ተላልፎ ከተገኘ የያዘውን ነዳጅ ለመንግሥት እንዲወረስ በማድረግ ተግባራዊ ያደርጋል፤

4/ ከየዞኑ፣ ከየወረዳው እና ከየክፍለ-ከተማው የነዳጅ ውጤቶች ስርጭት እና ግብይት መረጃ በማሰባሰብ በየወሩ እና በየሩብ ዓመቱ ለባለሥልጣኑሪፖርት ይልካል።

## 12. <u>በባለሥልጣኑ የሚመደብ ተቆጣጣሪ ስለሚያደርገው ቁጥጥር</u>

በባለሥልጣኑ የሚመደብ ማንኛውም የነዳጅ ውጤቶች ግብይትና ስርጭት ተቆጣጣሪ፡-

1/ ዘወትር በመንግሥት የሥራ ሠዓት በባለሥልጣኑ የተሰጠውን የመታወቂያ ወረቀት በማሳየት ወይም አጠራጣሪ ሁኔታ ሲያጋጥም ከመንግሥት የሥራ ሠዓት ውጪ ከመታወቂያው በተጨማሪ ከባለሥልጣኑ የተጻፈ የሥራ ስምሪት ደብዳቤ በማሳየት በማንኛውም የነዳጅ አስመጪ፣ አከፋፋይ፣ የነዳጅ ማደያ፣ አጓጓዥ እና የችርቻሮ መሸጫ ያለ ምንም ቅድመ ማስጠንቀቂያ በመግባት አዋጁን እና ይህን መመሪያ ለማስፈጸም ቁጥጥር ያካሂዳል፤

2/ ቁጥጥር የሚደረግባቸውን የግብይት ተዋናዮች እና የነዳጅ ውጤቶች በተመለከተ እንደ አስፈላጊነቱ ናሙናዎችን፣ ልኬቶችን፣ ፎቶግራፎችን፣ የቪዲዮ ቅጂዎችን ወይም የሰነድ ግልባጮችን ጨምሮ በእነዚህ ሳይወሰን ተቀባይነት ያላቸውን ሌሎች ማስረጃዎች ያሰባስባል፣ ለባለሥልጣኑ ያቀርባል፤

3/ በቁጥጥር ወቅት ያገኘውን ግኝት በተመለከተ ከድርጅቱ ህጋዊ ተወካይ ጋር በቸክሊስት ተፈራርሞ ቅጅውን ለድርጅቱ በመስጠት ለባለሥልጣኑ ሪፖርት ያቀርባል፤

4/ ቁጥጥር በሚያደርግበት ወቅት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከአካባቢው ፖሊስና ከሌሎችም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የጸጥታና የአስተዳደር አካላት ድጋፍ ይጠይቃል።

## 13. <u>አግባብነት ባለው አካል ስለሚመደብ ተቆጣጣሪ</u>

1/ አግባብነት ያለው አካል አዋጁን እና ይህን መመሪያ ለማስፈጸም በክልሉ እና በየደረጃው በሚገኙ የንግድ ጽህፈት ቤቶች ተቆጣጣሪዎችን ሊመድብ ይችላል፡፡

2/ ተቆጣጣሪው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 12 የተመለከቱትን የቁጥጥር ተግባራት በክልሉ ውስጥ ያከናውናል፡፡

**14. <u>የተቆጣጣሪ ኃላፊነት እና ተጠያቂነት</u>**

1/ ማንኛውም በባለሥልጣኑ ወይም አግባብነት ባለው አካል የሚመደብ ተቆጣጣሪ የሚከተለው ኃላፊነትና ተጠያቂነት ይኖረዋል፡-

ሀ) የቁጥጥር ተግባሩን ከመጀመሩ በፊት ቁጥጥር ለሚደረግበት የግብይት ተዋናይ የመታወቂያ ወረቀት ወይም የስምሪት ደብዳቤ ወይም እንደነገሩ አግባብነት ሁለቱንም የማሳየት፤

ለ) የአዋጁ እና የዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች መጣሳቸውን ሲያውቅ ወዲያውኑ ሪፖርት የማቅረብ፤

ሐ) በሥራ አጋጣሚ ያገኘውን ማንኛውንም መረጃ ወይም ሰነድ በሚስጢር የመጠበቅ፤

መ) ለራሱ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ ከሚቆጣጠረው የግብይት ተዋናይ ምንም ዓይነት የገንዘብ ክፍያ ወይም የተስፋ ቃል አለመጠየቅ፡፡

2/ ማንኛውም ተቆጣጣሪ የዚህን አንቀጽ ድንጋጌዎች ተላልፎ ከተገኘ አግባብነት ባለው የመንግሥት ሠራተኞች ሕግ መሠረት በዲሲፕሊን ተጠያቂ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ ድንጋጌ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ስለ አስተዳደራዊ እርምጃዎች እና ስለ ቅሬታ አቀራረብ</u>

**15. <u>በአስመጪ ላይ ስለሚወሰድ አስተዳደራዊ እርምጃ</u>**

1/ ማንኛዉም አስመጪ የዚህን መመሪያ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (1) ፣ (2) ፣ (3) ወይም (7) ድንጋጌዎች ተላልፎ የተገኘ እንደሆነ የተቋሙ ኃላፊ ተጠያቂ እንዲሆን ባለሥልጣኑ አስመጪው ተጠሪ ለሆነለት አስፈጻሚ አካል እና ለሚኒስትሩ በጽሁፍ ሪፖርት ያደርጋል፡፡

2/ አስመጪው የዚህን መመሪያ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (4)፣ (5) ወይም (6) ድንጋጌዎች ተላልፎ የተገኘ እንደሆነ ባለሥልጣኑ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፡፡

## 16. <u>በአከፋፋይ ላይ ስለሚወሰድ አስተዳደራዊ እርምጃ</u>

1/ ማንኛውም አከፋፋይ፡-

ሀ) የዚህን መመሪያ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (1) ፣ (2) ፣ (3) ፣ (5) ፣ (8) ፣ (9) ፣ (11) ወይም (12) ድንጋጌዎች ተላልፎ የተገኘ እንደሆነ ለ30 ተከታታይ ቀናት የነዳጅ ኮታው እንዳይሰጠው በመከልከል ይቀጣል፤

ለ) የዚህን መመሪያ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (4) ፣ (6) ወይም (7) ድንጋጌዎች ተላልፎ የተገኘ እንደሆነ ለ15 ተከታታይ ቀናት የነዳጅ ኮታው እንዳይሰጠው በመከልከል ይቀጣል፤

ሐ) የዚህን መመሪያ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (10) ወይም ከ (13) እስከ (19) ከተመለከቱት ድንጋጌዎች አንዱን ተላልፎ የተገኘ እንደሆነ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፤

መ) ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (ሀ)፣ (ለ) ወይም (ሐ) የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ለሁለተኛ ጊዜ ተላልፎ የተገኘ እንደሆነ ለ90 ተከታታይ ቀናት የብቃት የምስክር ወረቀቱ ይታገዳል፤

ሠ) ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (መ) መሠረት አስተዳደራዊ እርምጃ ከተወሰደበት በኋላ በአንቀጽ 5 የተጣለበትን ማንኛውንም ግዴታ ተላልፎ የተገኘ እንደሆነ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ ይሰረዛል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ለተመለከቱት አስተዳደራዊ እርምጃዎች አፈጻጸም ባለሥልጣኑ ለአስመጪው በጽሁፍ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

## 17. <u>በነዳጅ ማደያ ላይ ስለሚወሰድ አስተዳደራዊ እርምጃ</u>

1/ ማንኛውም ነዳጅ ማደያ፡-

ሀ) የዚህን መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) ተላልፎ የተገኘ እንደሆነ በ180 ቀናት ውስጥ አስፈላጊውን ማስተካከያ እስኪያደርግ ድረስ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ ይታገዳል፤

ለ) የዚህን መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (3) ወይም (4) ተላልፎ የተገኘ እንደሆነ ለ60 ተከታታይ ቀናት የነዳጅ ኮታው እንዳይሰጠው በመከልከል ይቀጣል፤

ሐ) የዚህን መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (5)፣ (6) ወይም (10) ተላልፎ የተገኘ እንደሆነ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ ለ180 ተከታታይ ቀናት ይታገዳል፤

መ) የዚህን መመሪያ አንቀጽ 6 ከንዑስ አንቀጽ (7) እስከ (9) ከተመለከቱት ድንጋጌዎች አንዱን ተላልፎ የተገኘ እንደሆነ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፤

ሠ) አዲስ ግንባታ አጠናቆ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በተሰጠው ተከታታይ 90 ቀናት ውስጥ ወደ ሥራ ያልገባ እንደሆነ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ ለአንድ ዓመት ይታገዳል፤

ረ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (ሀ) መሠረት ለተወሰደው አስተዳደራዊ ርምጃ በ180 ቀናት ውስጥ አስፈላጊውን ማስተካከያ በማድረግ ዕገዳው እንዲነሳለት በጽሁፍ ካልጠየቀ ወይም በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 የተጣለበትን ማናቸውም ግዴታ ለሁለተኛ ጊዜ ተላልፎ የተገኘ እንደሆነ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ ይሰረዛል።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ለተመለከቱት አስተዳደራዊ እርምጃዎች አፈጻጸም ባለሥልጣኑ ለአስመጪው እና ለአከፋፋዩ በጽሁፍ ትእዛዝ ይሰጣል።

## 18. <u>በነዳጅ አጓጓዥ እና የባለንብረቶች ማህበር ላይ ስለሚወሰድ አስተዳደራዊ እርምጃ</u>

1/ ማንኛውም ነዳጅ አጓጓዥ ወይም የባለንብረቶች ማህበር ፡-

ሀ) በአንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (1)፣ (2)፣ (3) ወይም (6) የተደነገጉትን ግዴታዎች ተላልፎ የተገኘ እንደሆነ ወይም የመደበው የነዳጅ ማጓጓዣ አሽከርካሪ በአንቀጽ 8 ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (3) ከተመለከቱት ግዴታዎች አንዱን ተላልፎ የተገኘ እንደሆነ ለ180 ተከታታይ ቀናት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን በማገድ አገልግሎት እንዳይሰጥ ይደረጋል፤

ለ) በአንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (4)፣ (5) ወይም ከ (7) እስከ (10) ከተደነገጉት ግዴታዎች አንዱን ተላልፎ የተገኘ እንደሆነ ወይም የመደበው የነዳጅ ማጓጓዣ አሽከርካሪ በአንቀጽ 8

ከንዑስ አንቀጽ (4) እስከ (6) ከተመለከቱት ግዴታዎች አንዱን ተላልፎ የተገኘ እንደሆነ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፤

ሐ) የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በተሰጠው 90 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ሥራ ያልጀመረ እንደሆነ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ ለአንድ ዓመት ይታገዳል፤

መ) ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (ሀ) ወይም (ለ) የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ለሁለተኛ ጊዜ ተላልፎ የተገኘ እንደሆነ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ ይሰረዛል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ለተመለከቱት አስተዳደራዊ እርምጃዎች አፈጻጸም ባለሥልጣኑ ለአስመጪው እና ለአከፋፋዩ በጽሁፍ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

## 19. <u>በነዳጅ ማጓጓዣ አሽከርካሪ ላይ ስለሚወሰድ አስተዳደራዊ እርምጃ</u>

ማንኛውም የነዳጅ ማጓጓዣ አሽከርካሪ በአንቀጽ 8 የተደነገጉትን ማናቸውም ግዴታዎች ተላልፎ የተገኘ እንደሆነ ባለሥልጣኑ፡-

1/ የመጀመሪያ ጥፋት ሲሆን አጓጓዡ ተገቢውን እርምጃ እንዲወስድ በጽሁፍ ያሳውቀዋል፤

2/ የተጣለበትን ግዴታ ለሁለተኛ ጊዜ ተላልፎ የተገኘ እንደሆነ አሽከርካሪው ለሚያንቀሳቅሰው ማንኛውም የነዳጅ ማጓጓዣ የጭነት አገልግሎት እንዳይሰጥ ለአከፋፋዩ እና ለአስመጪው በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡

## 20. <u>ስለ ቅሬታ አቀራረብ እና ውሳኔ አሰጣጥ</u>

1/ በዚህ መመሪያ በሚሸፈን ማናቸውም ጉዳይ ላይ በሚመለከተው የሥራ ኃላፊ በተሠጠ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው ውሳኔ በተሰጠ በ10 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን በጽሁፍ ለባለሥልጣኑ የበላይ ኃላፊ ማቅረብ ይችላል፡፡

2/ የባለሥልጣኑ የበላይ ኃላፊ ቅሬታ በቀረበ በ15 የሥራ ቀናት ውሥጥ ውሳኔውን በጽሁፍ ለቅሬታ አቅራቢው ማሳወቅ አለበት፡፡

3/ የባለሥልጣኑ የበላይ ኃላፊ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ምላሽ ያልተሰጠው ማንኛውም ሰው በ10 ተከታታይ ቀናት ውስጥ አቤቱታውን በጽሁፍ ለሚኒስቴሩ የበላይ ኃላፊ ማቅረብ ይችላል፡፡

4/ የሚኒስቴሩ የበላይ ኃላፊ አቤቱታ በቀረበ በ15 የሥራ ቀናት ውሥጥ ውሳኔውን በጽሁፍ ለቅሬታ አቅራቢው ማሳወቅ አለበት፡፡

5/ የሚኒስቴሩ የበላይ ኃላፊ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ምላሽ ያልተሰጠው ማንኛውም ሰው በ60 ቀናት ውስጥ አግባብ ላለው ፍርድ ቤት አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፡፡

# ክፍል አምስት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 21. የመተባበር ግዴታ

1/ ማንኛውም የግብይት ተዋናይ በዚህ መመሪያ መሠረት ለሚደረገው የቁጥጥር ሥራ አስፈላጊውን ትብብር የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

2/ ፖሊስና ሌሎችም ጉዳዩ የሚመለከታቸው የጸጥታና የአስተዳደር አካላት ይህን መመሪያ በማስፈጸም ሂደት ልዩ ትብብር የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## 22. የተሻሩ እና ተፈጻሚነት የሌላቸው መመሪያዎች

1/ የነዳጅ ውጤቶች የሥርጭት፣ የርክክብና የሽያጭ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 904/2014 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

2/ ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ እና ልማዳዊ አሠራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## 23. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ከተመዘገበበት እና በሚንስቴሩ ይፋዊ ድረ-ገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ፣ ሰኔ 2017 ዓ.ም

ካሳሁን ጎፌ ባለሚ (ፒ.ኤች. ዲ)

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ሚኒስትር